**መመሪያ ቁጥር 01/ 2000 ዓ.ም**

# የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት መመሪያ

የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ኅብረተሰቡን በማስተማር፣በማዝናናት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት አማራጭ የብሮድካስት አገልግሎት በመሆኑ፣ ይህንኑ አገልግሎት ማሳደግና ማስፋፋት በማስፈለጉ፣

የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ተደራሽነትን በማመጣጠን እና ፍትሐዊ ውድድርን በማስፈን ውስን የሆነውን የሬድዮ ሞገድ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

አገልግሎቱን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው የፈቃድ አሰጣጥና አሠራር ሥርዓት መምራት በማስፈለጉ፣ በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/99 አንቀጽ 47 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 01 / 2000 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. "የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ትርፍን መሠረት ያደረገ፣ ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅና ለማዝናናት ሕጋዊ ሰውነት ባለው ድርጅት የተቋቋመ የሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡
2. "አመልካች" ማለት የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ያመለከተ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ለንግድ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡
3. "ባለፈቃድ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ወይም ቀደም ሲል በህጋዊ መንገድ የተቋቋመ የንግድ ሬዲዮ ድርጅት ነው፡፡
4. "የፈቃድ ቡድን" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለመውሰድ የሚፈልጉ አመልካቾችን የሚጋብዝ፣ ፈቃዱን ለማግኘት የቀረቡ ማመልከቻዎችን የሚመዘግብ፣ ማመልከቻዎችን በማጣራት

ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ሲፈቀድም ፈቃዱን የሚሰጥና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የሚያከናውን የተለያዩ ባለሙያዎች ያሉበት ቡድን ነው፡፡

5. "የበላይ ኃላፊ" ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ም/ዋ/ዳይሬክተር ነው፡፡
6. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47/1/ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
7. "አገር አቀፍ ስርጭት" ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍን የንግድ ሬድዮ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡
8. "ክልላዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡
9. "አካባቢያዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ወረዳ ወይም ማዘጋጃ ቤት ብቻ የተወሰነ የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡
10. "አገራዊ ፕሮግራም" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያዊያን የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው፡፡
11. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ነው፡፡
12. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ቦርድ ነው
13. "ሚኒስቴር" ማለት የማስታወቂያ ሚኒስቴር ነው፡፡
14. "አዋጅ" ማለት ስለብሮድካስት አገልግሎት የወጣው አዋጅ ቁጥር 533/99 ነው፡፡
15. "ሰው" ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የፈቃድ አሰጣጥ

### 3. የፈቃድ አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡
2. አንድ ባለፈቃድ በአንድ ፈቃድ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይችልም ፡፡

## 4. የማመልከቻ ቅጽ፣

1. የአመልካቹን ስምና አድራሻ፣
2. የፕሮግራሙን ዓላማ፣ ምንጮች እና የስርጭት ፕሮግራሙን ቀንና ሰዓት፣
3. ለስርጭቱ የሚውለውን የመሣሪያ ዓይነትና ጉልበት፣
4. የማሰራጫ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን /የሚቋቋሙበትን/ ቦታ፣
5. ሥራውን ለማቋቋምና ለማካሄድ የሚያስፈልገውን የገንዘብ /ካፒታል/ መጠን፣
6. ሌሎች አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፣

ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 5. ከማመልከቻው ቅጽ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

1. የአመልካቹ መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
2. የአገልግሎቱ የፕሮጀክት ጥናት /ሰነድ/፣
3. የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ፣
4. የጣቢያውን ሥራ ሊያካሂዱ የሚችሉ የሥራ መሪዎች የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ፣
5. የማሰራጫ አገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅር፣የባለሙያዎች የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና የሥራ መደብ፣
6. ሌሎች አመልካቹ ይጠቅማሉ ብሎ የሚያቀርባቸው ሰነዶች፣

በአባሪነት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

## 6. አመልካቾችን ስለመጋበዝ

6.1.ባለሥልጣኑ የንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾችን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች የመገናኛ ብዙኃን በሚገለጽ ማስታወቂያ ይጋብዛል፡፡ ማስታወቂያውም:-

1. ሊፈቀድ የታሰበውን የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነት፣
2. አገልግሎቱ የሚሸፍነውን አካባቢ፣
3. ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፣
4. የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ፣ እና
5. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፣

ይይዛል፡፡

6.2. የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው እንደተጠናቀቀ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የአመልካቾችን ዝርዝርና ስለአመልካቾች መጣራት የሚገባቸውን ጉዳዮች በመገናኛ ብዙኃን በመግለጽ ኀብረተሰቡ አስተያየቱን እንዲሰጥ ይጋብዛል፡፡

6.3. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹን አስመልክቶ ኀብረተሰቡ ባቀረባቸው አስተያየቶች ላይ ባለሥልጣኑ አመልካቹን ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

## 7. ተቀባይነት ስለሌው ማመልከቻ

አንድ አመልካች፣

1. የካፒታል ምንጩን ሕጋዊ ማስረጃ ካላቀረበ፣
2. ከማመልከቻ ቅጹ ጋር የፕሮጀክት ፕሮፖዛል አያይዞ ካላቀረበ፣
3. የካፒታል ማረጋገጫ ሰነድ ካላቀረበ
4. በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው ሰው ከሆነ፣

ዝርዝር ማጣራት  ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል፡፡

## 8. የማወዳደሪያ መስፈርቶች

8.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9/2/ መሠረት የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለÕ አመልካቾች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት ይወዳደራሉ::

1. አገልግሎቱን ለመስጠት የፋይናንስ አቅም ተአማኒነትና ብቃት፣
2. በአመልካቹ ፕሮጀክት የተዘረዘሩ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፣
3. አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ድርጅታዊ ብቃት፣ እውቀትና የሥራ ልምድ፣
4. በአመልካቹ የቀረበው የፕሮግራም ይዘትና በፕሮግራሙ የተካተቱ ማኀበራዊ ፍላጎቶች፣
5. ለአገልግሎቱ የተመደበው የስርጭት ጊዜ፣

8.2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ መስፈርቶች በሚመለከት ዝርዝር መስፈርቶችን  ባለስልጣኑ ያወጣል፡፡

## 9. የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1. የፈቃድ ቡድን በአንቀጽ 10 መሠረት የመጀመሪያ ማጣሪያ አድርጎ ውጤቱን ከማብራሪያ ጋር ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፣
2. የበላይ ኃላፊው፣ ከቡድኑ የቀረበለትን የአመልካቾች ዝርዝርና ማብራሪያ በመመርመር ወደ ሁለተኛው ዙር ማጣሪያ ማለፍ የሚገባቸውን በመወሰን ለቡድኑ ይልካል፣
3. የፈቃድ ቡድኑም በአንቀጽ 8 በተጠቀሰው የማወዳደሪያ መስፈርት መሠረት በማጣራት ፈቃድ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸውን በመለየት ለበላይ ኃላፊው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣
4. የበላይ ኃላፊው ፈቃድ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸውን በመለየት ውሳኔ ይሰጣል፣
5. የበላይ ኃላፊው ውሳኔ ለአመልካቾች ይገለጽላቸዋል፣
6. ፈቃድ እንዲሰጣቸው የተወሰነላቸው አመልካቾች ለፈቃዱ የተተመነውን ክፍያ ከፍለው ፈቃዱን እንዲወስዱ በጽሑፍ ይገለጽላቸዋል፣
7. ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት፣ በጊዜው ቀርበው ክፍያውን ለፈጸሙ እና በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ሰነድ የፈረሙ አመልካቾች ፈቃዱ ይሰጣቸዋል።
8. ፈቃድ እንዲወስዱ በፅሁፍ የተገለጸላቸው አመልካቾች ደብዳቤው በደረሳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈጸምና በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም ፈቃዱን ካልወሰዱ የተሰጠው የፈቃድ ውሳኔ ይሰረዛል።
9. ፈቃድ ያላገኙበትን ምክንያት ማወቅ ለሚፈልጉ አመልካቾች ባለሥልጣኑ ምክንያቱን በግልጽ ያሳውቃል፣
10. ፈቃድ የተከለከለ አመልካች በበላይ ኃላፊው ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ14 (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል። ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ20 (ሃያ) ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጠዋል፣
11. ማንኛውም ባለፈቃድ፣ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ እንደአግባብነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## የፈቃድ ቡድን

### 10. የፈቃድ ቡድኑ  ተግባርና ኃላፊነት

የባለሥልጣኑ የፈቃድ ቡድን፣

1. ፈቃድ ጠያቂ አመልካቾች ሞልተው የሚያቀርቡትን የማመልከቻ ቅጽና አባሪ ሰነዶች ይቀበላል፣ ይመዘግባል፣ ለዚሁም ማስረጃ ይሰጣል፤
2. የመዘገባቸውን አመልካቾች ዝርዝር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አመቺ በሆኑ የመገናኛ ብዙኋን ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ስለአመልካቾች ከሕዝብ አስተያየት ይሰበስባል፤
3. መዝግቦ የተቀበላቸውን የማመልከቻ ቅጾችና አባሪ ሰነዶች እንደዚሁም የሕዝብ አስተያየቶች በአግባቡ ይይዛል፤
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት በማመልከቻዎች ላይ የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር የአመልካቾችን ዝርዝር ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፤
5. በበላይ ኃላፊው ውሳኔ መሰረት የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለፉ አመልካቾችን ዝርዝር ይፋ ያደርጋል፡፡
6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት ዝርዝር ማጣራት በማድረግና በመለየት ከአስፈላጊ ማብራሪያ ጋር የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፤

## ክፍል አራት

## ባለፈቃድ

### 11. የባለፈቃዱ ተግባርና ኃላፊነት

ባለፈቃዱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ፈቃድ ባወጣበት የሬድዮ ጣቢያ ብቻ ፕሮግራሙን የማካሄድ፣
2. ለወሰደው ፈቃድ ተገቢውን ክፍያ የመፈጸም፣
3. የአገሪቱን የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ፣ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና ሚኒስቴሩ የሚያወጣቸውን የተለያዩ መመሪያዎች የማክበር፣
4. በሚኒስቴሩ የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጥ ሥርዓት የመዘርጋት፣
5. በጣቢያው የሚቀጠሩ ባለሙያዎች የውጭ አገር ዜጎች ከሆኑ፣

በቅድሚያ የሥራ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት የማውጣት፣

6. የዓለም አቀፍ የቴሌኮሚኒኬሽን ኅብረት በየጊዜው የሚያወጣውን ደንብ የማሟላት፣
7. የሬድዮ ጣቢያውን የሂሣብ መረጃ በአግባቡ የመያዝ፣
8. ባለሥልጣኑ በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ በስተቀር ፈቃድ ባወጣበት የመሣሪያ አይነትና ጉልበት ብቻ የማሰራጨት፣
9. የጣቢያውን የሥራ አመራርና ሠራተኞች በተመለከተ መረጃ የመያዝ ባለሥልጣኑ ሲጠይቅም በማንኛውም ጊዜ የማቅረብ፣
10. በተፈቀደለት የስርጭት ሰዓት በሙሉ የመጠቀም፣
11. ፈቃድ በወሰደበት አካባቢ የሚገኘውን ኅብረተሰብ በእኩልነት የማስተናገድ፤
12. ፈቃድ ለወሰደበት አካባቢ አገልግሎቱን የማድረስ፣
13. በሃሮግራሙ ውስጥ አካባቢያዊና አገራዊ ዜናዎችን የማካተት፣

## 12. ባለፈቃዱ በማመልከቻው ስለገለጻቸው የፈቃድ ሁኔታዎች

1. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው የገለጻቸው ሁኔታዎች የፈቃድ ግዴታ ሆነው ይቀጥላሉ፣
2. ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ በማመልከቻው የገለጻቸውን ሁኔታዎች መሠረት ያደረገ የፈቃድ ሁኔታዎች ሰነድ በማዘጋጀት ባለፈቃዱን ያስፈርማል።

## 13. የፈቃድ ዘመን

ለንግድ ሬድዮ ብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጠው የፈቃድ ዘመን፣

1. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራጭ ከሆነ 8 ዓመት፣
2. በክልል ደረጃ የሚሰራጭ ከሆነ 10 ዓመት፣
3. የስርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ከሆነ 12 ዓመት፣
4. የስርጭት ሽፋኑ በአዲስ አበባና አካባቢዋ ከሆነ 6 ዓመት፣
5. የስርጭት ሽፋኑ በድሬዳዋ የተወሰነ ከሆነ 10 ዓመት፣

ይሆናል።

# <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ክፍያ</u>

### 14. <u>ስለ ክፍያ ዓይነት</u>

1. ማንኛውም አመልካች የማመልከቻ ክፍያ፣ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃድ ሲወሰድ የፈቃድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የእድሳት ክፍያ ይከፍላል።
2. የክፍያው መጠን በባለሥልጣኑ ይወሰናል።

### 15. <u>ስለ ክፍያ ጊዜ</u>

1. አመልካቹ የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ሲያቀርብ የማመልከቻ ክፍያ ይፈጽማል።
2. ባለፈቃዱ የፈቃድ የምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት የፈቃድ ክፍያ ይፈጽማል።
3. ባለፈቃዱ ዓመታዊ ክፍያውን የመንግሥት በጀት ዓመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ካልከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር አምስት በመቶ /5%/ መቀጫ እየታከለበት ይከፍላል። ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ አምሣ በመቶ/50%/ ሊበልጥ አይችልም።

# <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ፈቃድ ማገድ፤መሰረዝና ቅሬታ አቀራረብ</u>

### 16. <u>ፈቃድ ስለማገድ</u>

1. የአዋጁንና የዚህን መመሪያ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን የጣሰ ባለፈቃድ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ ሊታገድበት ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረግ ዕግድ በጽሑፍ ሆኖ ዕግዱ የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው ይደረጋል።
3. የዕግዱ ምክንያት በባለሥልጣኑ በተገለጸለት በ15 ቀናት ውስጥ ባለፈቃዱ የዕግዱን ምክንያት ካስወገደ ይህንኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
4. የዕግዱ ምክንያት የተወገደ መሆኑን ባለሥልጣኑ ካረጋገጠ ዕግዱን ያነሳለታል።

## 17. ፈቃድ ስለመሰረዝ

17.1 የባለፈቃዱ ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊሰረዝ ይችለል፣

1. ባለፈቃዱ ፈቃድ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ስርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
2. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው ያለአግባብ ወይም በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. የስርጭት ጣቢያው ያለበቂ ምክንያት ስርጭቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፣
4. ጣቢያው በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲዘጋ  ሲወሰን፣
5. ባለፈቃዱ በራሱ አነሳሽነት ፈቃድ ያወጣበትን ሥራ ሲያቆም፣
6. በአዋጁ አንቀጽ 30/4/ የተደነገጉትን ተላልፎ ሲገኝ፣
7. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሠረት ክፍያ ያልፈጸመ እንደሆነ፣
8. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16(3) መሠረት የዕግዱ ምክንያት መወገዱን በጽሑፍ ያላረጋጠ ከሆነ፣

17.2  ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 17.1 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃድ ሲሰረዝ፣ ባለሥልጣኑ ይህንኑ በጽሑፍ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 18. ቅሬታ ስለማቅረብ

1. ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ መሆኑን ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ካስታወቀው ቀን ጀምሮ በ14 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ቦርድ  በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቦርዱም ለቀረበለት ቅሬታ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

# ክፍል ሰባት

## የሚደረጉ ለውጦችን ማስፈቀድና ማሳወቅ

## 19. ስለማስፈቀድ

ባለፈቃዱ የሚከተሉትን የቴክኒክ እና ሌሎች ለውጦች ሲያደርግ ባለሥልጣኑን አስቀድሞ ማስፈቀድ አለበት፡፡

1. የማሰራጫ መሣሪያውን ጉልበት ከተፈቀደው መጠን በላይ ወይም በታች ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ሲፈልግ፣
2. የአንቴናውን ዓይነትና ርዝመት ላይ ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ፣
3. የማሰራጫ መሳሪያውንና የአንቴናውን ቦታ መቀየር ሲፈልግ፣
4. የአንቴና ምሰሶ ከፍታ መጨመር ሲፈልግ፣
5. ከንብረት ይዞታ ጋር የተያያዙ ውሎችን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሰረዝ ሲፈልግ፣
6. ማንኛውም የአክሲዮን ድርሻ ለውጥ ማድረግ ወይም ለሌላ ማስተላለፍ ሲፈልግ፣
7. የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ ብሮድካስተሮች የሚያስተላልፉትን ፕሮግራም ተቀብሎ በሬዲዮ ጣቢያው ማሰራጨት ሲፈልግ፡፡

## 20. ስለማሳወቅ

ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ሲያደርግ ለውጦችን ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

1. በመሣሪያ ብልሽት የስርጭት አገልግሎት ለአንድ ወር ሲቋረጥ፣
2. የፕሮግራም ዳይሬክተር ሲያስናብት ወይም የዳይሬክተር ለውጥ ሲያደርግ፣
3. የፕሮግራምና የስርጭት ሰዓት ለውጥ ሲያደርግ፣
4. የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ፣

# ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. ስለ አገራዊ፣ክልላዊና አካባቢያዊ የስርጭት ጣቢያ ፕሮግራም

1. አገር አቀፍ ጣቢያ ከሆነ፡-
   ከሣምንታዊ ስርጭት ጊዜው ውስጥ ቢያንስ ስድሣ በመቶ /60%/ ለአገራዊ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡
2. ክልላዊ ጣቢያ ከሆነ፡-
   ከሣምንታዊ የስርጭት ጊዜው ቢያንስ ስድሣ በመቶውን /60%/ ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች መዋል አለበት፡፡
3. በአካባቢ ደረጃ የሚቋቋም ጣቢያ ከሆነ ፡-
   ከሣምንታዊ የስርጭት ጊዜው ውስጥ ቢያንስ ስድሣ በመቶውን /60%/ አካባቢውን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

### 22. ፋይል ተደርገው መያዝ ስላለባቸው ጉዳዮች

የአዋጁ አንቀጽ 38 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃድ ዘመኑ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ፋይል አድርጎ መያዝ ይኖርበታል፡፡

1. የቢዝነስ እና ዓመታዊ የበጀት ዕቅዶች፣
2. የሂሣብ መዝገቦችና ዓመታዊ ኦዲት ሪፖርቶች፣
3. በባለፈቃዱ የተከናወኑ የኢንቨስትመንት ተግባራት፣
4. በባለፈቃዱ ወይንም ባለፈቃዱን በመወከል የተደረጉ ውሎችና ስምምነቶች፣
5. የለጋሾች ዝርዝር እና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ዝርዝር፣
6. የሠራተኞች የሥራ ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመን እና በባለፈቃዱ የተነደÕ የሥልጠና መርሀ ግብሮች ዝርዝር፣
7. የፕሮግራም መርሀ ግብሮችና የተደረጉ ማሻሻያዎች፣

## 23. የሬድዮ ጣቢያውን ለሌላ ማስተላለፍ ስላለመቻሉ

1. ባለፈቃዱ ያገኘውን ፈቃድ ወይም በፈቃዱ ውስጥ የተሰጡ ማናቸውንም መብቶች ለሌላ ወገን ማዛወር፣ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም ማስያዝ አይችልም።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ሥራውን ማካሄድ ካልቻለ ፈቃዱን በመመለስ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ሲፈቀድለት መሣሪያውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ይችላል።

## 24. የተሻረ መመሪያ

የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/ 1997 ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽረዋል

## 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሻል ይችላል።

## 26. መመሪያው የጸና ስለመሆኑ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርሃን ኃይሉ

የማስታወቂያ ሚኒስቴር